# የኢትዮጵያ አገር አድን በዲሞክራሲ የጋራ ንቅናቄን ምሥረታ በማስመልከት የወጣ ድርጅታዊ መግለጫ

**ማክሰኞ ጳጉሜ 3 ቀን 2007 ዓም**

የኢትዮጵያ ሕዝብ የአገሩን ሉዓላዊነት እና አንድነት አስከብሮ የኖረ ብቻ ሳይሆን አፍሪካዉያን ወንድሞቹና እህቶቹ ከቅኝ አገዛዝ ነፃ እንዲወጡ የራሱን አስተዋጽኦ ያደረገ ጀግና ሕዝብ ነዉ። ሆኖም ይህ ጀግና ሕዝብ ከአብራኩ በወጡ ገዢዎች ነፃነቱ ተገፎ፤ መብቶቹ ተረግጠው የመከራ ኑሮ እየገፋ አያሌ ዘመናት ኖሯል። ይህ የመከራና የሰቆቃ ኑሮ ዛሬም አላበቃም፤ እንዲያዉም "ከጭቆና ነፃ አወጣንህ" እያሉ የሚሳለቁበት ግፈኛ ገዢዎች የጫኑበትን የስቃይ ቀንበር ተሸክሞ የዉርደት ኑሮ እየኖረ ነዉ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የአገር ዉስጥ ገዢ መደቦች የጫኑበትን የስቃይና የመከራ ቀንበር ሰባብሮ ለመጣል፤ ፍትህ፣ ሰላምና እኩልነት የሰፈነበት ኑሮ ለመኖር ዓመታት የፈጀ ከፍተኛ መስዋዕትነት የተከፈለበት ትግል አድርጓል። እስካሁን ትግሉን በአሸናፊነት ተወጥቶ የናፈቀዉን ፍትህ፣ ሰላምና ብልጽግና ማግኘት አልቻለም። ለዚህ በርካታ ምክንያቶች ያሉት ቢሆንም ዋናዉ ምክንያት ሕዝባዊ ትግሉን በተባበረና በተቀናጀ መልክ መምራት አለመቻሉ ነዉ። ይህ ስር የሰደደ ያለመተባበር ችግር በህወሃት/ኢህአዴግ ዘመን ተባብሷል። ህወሃት/ኢህአዴግ ሆን ብሎ የፈጠረዉ የመለያየትና የከፋፍለህ ግዛዉ ፖሊሲ ለጋራ ድል አብሮ መታገልን በጭራሽ አስቸጋሪ ጉዳይ አድርጎት ቆይቷል።

ዛሬ ግን ይህ ሁኔታ ተቀይሯል። በጋራ አብሮ በመታገል የሚገኘዉ ዘርፈ ብዙ ጥቅም የገባቸዉና ካለፈዉ ተደጋጋሚ የታሪክ ስህተት የተማሩ፣ በአገራችን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲመሠረት በምድር ላይ በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ አራት ድርጅቶች በጥምረት ተሳስረው በጋራ ለመታገል ወስነዋል። እነዚህ አራት ድርጅቶች ለብዙ ዓመታት የአብሮ መታገል ፍላጎት እንቅፋት የሆነዉን የገዢ መደቦች የከፋፍለህ ግዛዉ ሴራ በጣጥሰዋል። ይህ ዛሬ በጥምረት የተጀመረው ትብብር እያደገ ሄዶ በአጭር ግዜ ዉስጥ ወደ ውህደት እንዲያድግ ይደረጋል። ከዚህም በተጨማሪ ንቅናቄው ከሌሎች ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት መመስረት ከሚታገሉ ኢትዮጵያውያን ድርጅቶች ጋር ተጣምሮ ለመስራት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ አጠንክሮ ይገፋበታል።

በዚህም መሠረት፣

1ኛ) የአፋር ድርጅቶች የጋራ ንቅናቄ

2ኛ) የትግራይ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ፣

3ኛ) የአማራ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ንቅናቄ፣ እና

4ኛ) አርበኞች ግንቦት 7: ለአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ፣

<u>**የኢትዮጵያ አገር አድን በዲሞክራሲ የጋራ ንቅናቄ (በአጭሩ "የአገር አድን ንቅናቄ")**</u> የሚባል ድርጅት ዛሬ በአዲስ ዓመት መባቻ ጳጉሜ 3 ቀን 2007 ዓ.ም. ፈጥረዋል። የንቅናቄውን ምክርቤት፤ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴና የተለያዩ መምሪያዎችን ከማቋቋሙም በላይ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ሊ/መንበር፤ አቶ ሞላ አስገዶምን ም/ሊቀመንበር አድርጎ መርጧል።

የኢትዮጵያ አገር አድን በዲሞክራሲ የጋራ ንቅናቄ ከአራቱ አባል ድርጅቶች የተውጣጣ ***አገር አድን ሠራዊት አቋቁሟል።*** ይህ አገር አድን ሠራዊት በሚያደርጋቸዉ የትግል እንቅስቃሴዎች ሁሉ የአራቱ አባል ድርጅቶች ሠራዊቶች አባላት ሁሌም ከጎኑ አብረዉ በመሠለፍ ይታገላሉ።

ባለፉት ሃያ አራት ዓመታት ከህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ በሰላማዊ መንገድ ለመገላገል የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፤ ሆኖም ለእነዚህ ጥረቶች ከአገዛዙ የተገኘዉ ምላሽ እስር፤ ስደት፤ ዉርደትና ሞት ብቻ ነው። ይህ በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይወድ የሕዝባዊ አመጽ አማራጭን እንዲቀበል ተገዷል። በዚህም ምክንያት አሁንም ለሰላም የዘረጋዉን እጅ ሳያጥፍ የህወሃት/ኢህአዴግን አገዛዝ በሕዝባዊ አመጽ ለማስወገድ የጋራ እንቅስቃሴዉን ጀምሯል።

ቢጋራ የሚደረገዉ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በትግሉ ሜዳ ከሚደረገው ሕዝባዊ አመጽ በተጨማሪ የፖለቲካ፤የዲፕሎማሲና የሕዝብ ግኙኝነት ዘርፎችን ያካተተ ይሆናል። ይህ አዲስ ጅምር የህወሓት/ኢህአዴግን አገዛዝ ዕድሜ ለማሳጠር በሚደረገዉ ሕዝባዊ ትግል ዉስጥ የመጀመሪያዉና ወሳኝ ምዕራፍ ሲሆን በዚህ አዲስ ጅምር ዉስጥ አገር አድን ሠራዊቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጉያ ዉስጥ እየገባ፤ ሕዝብን እያነቃና እያደራጀ ወገኑ ከሆነዉ ሕዝብ ጋር የሚያደርገዉ የትግል እንቅስቃሴ በመጪዉ አዲስ አመት በተጠናከረ መልኩ ይቀጥላል።

የኢትዮጵያ አገር አድን በዲሞክራሲ የጋራ ንቅናቄ፣ አገር አድን ሠራዊት መመሥረቱን በዚህ መግለጫ ሲያሳወቅ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጎኑ እንዲቆም ጥሪ ያደርጋል። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሰብዓዊ መብቶቹና ነፃነቱ ተከብረው በኢትዮጵያ ውስጥ በሰላም ሰርቶ መኖር የዜግነት መብቱ እንጂ የገዢዎች ችሮታ አለመሆኑን ማስመስከር አለበት። እኛ ኢትዮጵያዊያንን ለእስራት፤ ለስደትና ለሞት የዳረገን የዉርደት ኑሮ ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ማብቃት አለበት።

ይህንን ብሩህ ዓላማ እዉን የሚያደርግ ሁለንተናዊ የአገር አድን ትግል ተጀምሯል!!!

**የኢትዮጵያ ገበሬ ሆይ !**

መሬት የሕዝብ ነዉ እየተባልክ ህወሃት/ኢህአዴግ ሲያሰኘዉ አንተንና ቤተሰብህን ከመሬትህ እያፈናቀለና መሬቱን ለባዕዳን እየሸጠ፤ አለዚያም በገዛ መሬትህ ላይ እንደ ገባር ተቆጥረህ አገሪቱ የዝናብ እጥረት ባጋጠማት ቁጥር የዕርዳታ ሰጪዎችን እጅ ተመልካች ሆነሃል። ዛሬ ልጆችህ በአገር አድን እንቅስቃሴ ዙሪያ ተሰባስበዉ ከዚህ የዉርደት ኑሮ ነፃ ሊያወጡህ ቆርጠዉ ተነስተዋል። ይህ ትግል አንተ በምትኖርበት አካባቢ፣ በአንተ ድጋፍ እና አንተም ተሳትፈህበት የሚደረግ ትግል ነዉ። ስለዚህ ልጆችህ ከህወሓት/ኢህአዴግ ጋር በሚያደርጉት ትንንቅ መሸሸግያ ጫካቸዉ አንተ ነህ። ዉሃ ሲጠማቸዉ ውሃ እያጠጣህ፤ ሲርባቸዉ ቤት ያፈራዉን እያበላህ ይህንን ላንዴና ለመጨረሻ ግዜ የሚደረግ የመብት፤ የነፃነትና የእኩልነት ትግል ከልጆችህ ጋር አብረህ እንድትታገል በአገር አድን እንቅስቃሴዉ ዙሪያ የተሰባሰቡ ልጆችህ አገራዊ ጥሪ ያቀርቡልሃል።

## የኢትዮጵያ ወጣት ሆይ !

"የወደፊቷ ኢትዮጵያ ተረካቢ ነህ" እየተባለ በተደጋጋሚ እየተነገረህ ነዉ። አንተ በራስህ አይን እንደምትመለከተዉ የዛሬዋም ኢትዮጵያ ለአገርና ለሕዝብ ደንታ በሌላቸዉ ሰዎች እጅ ገብታ እየፈረሰች ነዉ። የዛሬዋ ኢትዮጵያ ከህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ነፃ ካልወጣች የነገዋ ኢትዮጵያ አትኖርም። የነገዋን ኢትዮጵያ መገንባት በአንተ በወጣቱ ጀርባ ላይ የወደቀ ኃላፊነት ነዉ፤ ይህ ሥራ የሚጀምረው ህወሓት/ኢህአዴግን ከሥልጣን በማባረር ነው። የስደት ኑሮ አብቅቶ በገዛ አገርህ ዉስጥ ባሰኘህ ቦታ ያሰኘህን ስራ እየሰራህ የክብር ኑሮ የምትኖርበትን ግዜ አንተዉ እራስህ ታግለህ ማምጣት አለብህ። ስለዚህ ዛሬ እራሳቸዉን አደራጅተዉ ከህወሓት/ኢህአዴግ ጋር ከሚፋለመው የአገር አድን ሠራዊት ጋር ዛሬውኑ ተቀላቀል፤ ይህንን ማድረግ የማትችል ደግሞ በምትኖርበት ቦታ ከምታምናቸዉ ጓደኞችህ ጋር ሆነህ እራስህን እያደራጀህና የመረጃ ማሰባሰብ ሥራዎችን እየሰራህ በየአካባቢህ የሚገኛዉን የሕዝባዊ እምቢ ተኝነት ትግል ተቀላቀል።

**በአገር ዉስጥና በዉጭ አገሮች ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የምትታገሉ ድርጅቶች ሆይ !**

ኢትዮጵያ ዉስጥ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ተገንብቶ ማየት የሚሹ የተለያዩ ድርጅቶች ህወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን ከመያዙ በፊትና ሥልጣን ከያዘም በኋላ በርካታ ዓመታት የፈጀ እልህ አስጨራሽ ትግል አካሂደዋል፤ ዛሬም እያካሄዱ ነዉ። ይህ በተናጠል እየተካሄደ ያለው ትግል በመካከላችን የልዩነትና ያለመተማመን አጥር ሰርቶ ስላራራቀን ህወሓት/ኢህአዴግን ማሸነፍ ቀርቶ ጠንካራ ጡንቻ እንድናሳርፍበት እንኳን አላስቻለንም። ይልቁንም የምንታገልለት ሕዝብ በየቀኑ ይታሰራል፤ ሰቆቃ ይፈፀምበታል፤ ይገደላል። ከዚህ ሁሉ ያመለጠዉ ደግሞ አገሩን ለቅቆ ይሰደዳል። በመካከላችን ያሉትን መለስተኛ ልዩነቶች ለሕዝብ አቅርበን በዲሞክራሲያዊ መንገድ ለመፍታት እስከተስማማን ድረስ የአሁኑ ትግላችን ይህንኑ ለማድረግ ነዉና ለዚህ እንቅፋት የሆነብንን የህወሓት/ኢህአዴግን ሥርዓት አብረን የማንታገልበት ምንም ምክንያት የለም። ስለሆነም ሁላችንም ፍሬያማ ለሆነ ትብብር እራሳችንን እናዘጋጅ፤ እንተጋገዝ።

**የኢትዮጵያ ምሁር ሆይ !**

አገራችን ኢትዮጵያ ሁለት እጆቿን ዘርግታ ከምንግዜዉም በላይ ያንተን የምሁር ልጆቿን የነቃ የትግል ተሳትፎ የምትፈልግበት ግዜ አሁን ነዉ። የኢትዮጵያ ምሁር ለኢትዮጵያ ሕዝብ መብትና ነፃነት መከበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፤ ግን ይህ በአብዛኛዉ በተናጠል

አንዳንዴም ድርጅታዊ መልክ ይዞ የተካሄደዉ ትግል የኢትዮጵያን ሕዝብ መብትና ነፃነት ማስከበር አልቻለም። በዚህ ተስፋ ቆርጠህ ከዳር ቆመህ የአገርህን ዉርደት ዝም ብለህ እያየህ ከነበርክ ይህ ከዳር ሆኖ የመመልከቻ ግዜ አሁን አብቅቷል። ስለዚህ አገር ዉስጥና ከአገርህ ዉጭ የምትኖረዉ ኢትዮጵያዊ ምሁር ከወንድሞችህና ከእህቶችህ ጋር በመሆን ይህንን የተቀጣጠለ ሕዝባዊ ትግል ተቀላቅለህ ዝንት አለም ስትመኘው የነበረውን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመመስረት የድርሻህን እንድታበረክት አገራዊ ጥሪ ቀርቦልሃል።

## የህወሓት/ኢህአዴግ አባላት ሆይ !

አንዳንዶቻችሁ ከልባችሁ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም የምትታገሉ መስሏችሁ፤ ከፊሎቻችሁ ደግሞ በሁኔታዎች ተገድዳችሁ፤ ሌሎቻችሁ ደግሞ አማራጭ አጥታችሁ ባለፉት ሃያ አራት ዓመታት ከለየለት የአገር ጠላት ድርጅት ጋር ተሰልፋችሁ እናት አገራችሁን ስትበድሉ ቆይታችኋል። ብዙዎቻችሁ የሕዝብ ስቃይና መከራ ተሰምቷችሁ የበደላችሁትን ሕዝብ ለመካስ አመቺ ግዜ እየጠበቃችሁ ነዉ ብለን እናምናለን። ደስ ይበላችሁ ያ የምትጠብቁት ግዜ ደርሷል። መጪዉ እዉነተኛ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እናንተንም ነፃ የሚያወጣ ሥርዓት ነዉና ሁላችሁም በያላችሁበት ትግሉን ተቀላቀሉ፤ መቀላቀል የማትችሉ ደግሞ መረጃ በማቀበልና ሥርዓቱን ከዉስጥ ሆናችሁ በማፍረስ ሕዝባዊዉን ትግል ደግፉ ከህሊናና ከታሪክ ተጠያቂነትም ራሳችሁን ታደጉ።

## የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ሆይ !

ያንተ ኃላፊነት የአገርህን ዳር ድንበር ከጠላት መጠበቅ ሆኖ ሳለ ህወሓት/ኢህአዴግ ግን በአገርህ አንድነት ላይ የሚሸርባቸዉ ሴራዎች አስፈጻሚ አድርጎህ ጭራሽ ደህንነቱን ለመጠበቅና ለመንከባከብ ቃል የገባህለት ህዝብ ላይ መሳሪያህን እንድታነሳ እያደረገህ ነዉ። አንተ የወጣኸዉ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አብራክ ዉስጥ ነዉ። ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ በዚህ ወልዶ ባሳደገህ ወገንህ ላይ ተኩስ የሚል ፀረ ሕዝብ ትዕዛዝ ሲሰጥህ በፍጹም አትቀበል፤ ይልቁንም ጠመንጃህን በጠላትህ በህወሓት/ኢህአዴግ ስርዓት ላይ አዙር ወይም መሳሪያህን እየያዝክ ወገኖችህን ተቀላቀል። እኛ ወገኖችህ ለነፃነት የምናደርገዉ ትግል በዘረፋና በሙስና ከከበሩ ዘራፊ ወታደራዊ መሪዎች ነን ባይ ሽፍቶች ጋር ነዉ እንጂ በፍጹም ካንተ ከወገናችን ጋር አይደለም። የእኛ ትግል አንተ የአገርህን ዳር ድንበር ለመጠበቅ የሚያስችልህን ብቃት ለመፍጠርና እዉነተኛ የሕዝብ ሠራዊት እንድትሆን ለማድርግ ነዉ እንጂ አንተን ወገናችንን ለመበታተን የመጣን ጠላቶች ወይም አንተን በመግደል የምንደሰት ብረት ነካሾች አይደለንም፡፡

## የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!

የባሰ የሚረግጥህና የሚጨቁንህ ሥርዓት በላይህ ላይ
አንድን ጨቋኝ አምባገነን ሥርዓት ታግለህ በደመሰስክ ማግሥት ከቀድሞው የባሰ የሚረግጥህና የሚጨቁንህ ሥርዓት በላይህ ላይ
እየተጫነ፤ ተቆጥረዉ የማያልቁ የስደት፣ የሰቆቃና የዉርደት ዓመታት አሳልፈሃል። አባቶችህ በደማቸዉ አስከብረዉ ያስረከቡህ የአገር አንድነት ላልቷል፤ አንተ ታግለህ ከቅኝ አገዛዝ ነፃ ያወጣሃቸዉ አገሮች በእድገት ወደኋላ ጥለዉህ ሄደዋል፤ የወለድካቸዉ ልጆችህ እስር ቤት ውስጥ ናቸዉ አልያም አንተንና አገራቸዉን ጥለዉ ተሰድደዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! "አምላኬ! አምላኬ! ይህ የመከራና የዉርደት ዘመን መቼ ይሆን የሚያበቃዉ?" እያልክ ሰማይ ሰማዩን እየተመለከትክ ፈጣሪህን ጠይቀሃል፤ ለምንህልም። ፈጣሪህ አልረሳህም። የወለድካቸዉ ልጆች ተሰባስበዉና ተደራጅተዉ የናፈቀህን የሰላምና የነፃነት ኑሮ የምታገኝበትን ቀን ለማቅረብ በአገር አድን ሠራዊትነት ተደራጅተው እየተፋለሙ ነዉ። የአገር አድን የጋራ ንቅናቄ ዓላማ አገራችን ኢትዮጵያ ፍትህ፤ ሰላምና እኩልነት የሰፈኑባት አገር እንድትሆን ነዉና፤ የምትችል በአካል ትግሉ ሜዳ ተገኝተህ በጉልበትህ፤ ይህን ማድረግ የማትችለዉ ደግሞ በገንዘብህ፤ በእዉቀትህና ለዚህ ከጠላት ጋር ለሚደረገዉ ትንንቅ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለወገን ኃይሎች በማቀበል ትግሉን ተቀላቀል።

**አንድነት ኃይል ነው!!!**

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**